## ትምህርት 34

1. እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን በሲና ተራራ ምን ሰጣቸው?

ሀ- አሥርቱን ትእዛዛት።

2. እግዚአብሔር ብቻ አምላካችን መሆን ያለበት ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም አምላክ አንድ ብቻ ስለ ሆነ ነው።

ለ- ምክንያቱም ሌላ አምላክ ስለሌለ ነው።

3. በእግዚአብሔር አምሳል ምስል መሥራት የሌለብን ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው።

ለ- እግዚአብሔር ሰውን እንስሳን ወይም ወፍን አይመስልም።

4. የእግዚአብሔርን ስም ማክበር ያለብን ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስምና እግዚአብሔር ስለማይነጣጠሉ ነው።

ለ- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ስምና እግዚአብሔር አንድ ስለሆኑ ነው።

5. በሳምንት አንድ ቀን ማረፍ ያለብን ለምድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን ስላረፈ ነው።

6. አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ማክበር ያለብን ለምንድን ነው?

ሀ- ምክንያቱም እኛን እንዲያሳድጉ እግዚአብሔር እነርሱን ስለሰጠን ነው።

7. እግዚአብሔር እንዳለው አንድን ሰው ከጠላነው ምን አደረግን ማለት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር አንድን ሰው ከጠላነው እንደገደልነው ተናግሮናል።

8. እግዚአብሔር እንዳለው ወንድ ሴትን አይቶ፥ ሴትም ወንድን አይታ አብረው ለመተኛት ከተመኙ ምን አደረጉ ማለት ነው?

ሀ- እግዚአብሔር እንዳለው ወንድ ሴትን አይቶ፥ ሴትም ወንድን አይታ አብረው ለመተኛት ከተመኙ ያን ጊዜ አመነዘሩ ማለት ነው።

9. እግዚአብሔር የአንድን ሰው ንብረት ለመስረቅ ካሰብን ምን አደረግን አለ?

ሀ- እግዚአብሔር የአንድን ሰው ንብረት ለመስረቅ ካሰብን እንደሰረቅን ተናግሯል።

10. እግዚአብሔር እውነትን እያወቅን የማንናገር ከሆነ ምን እያደረግን ነው አለ?

ሀ- እግዚአብሔር እውነትን እያወቅን የማንናገር ከሆነ ውሸታሞች ነን ብሏል።

11. የሌሎችን ንብረት መመኘት የሌለብን ለምንድን ነው?

ሀ- ለሌሎች ያላቸውን ነገር የሰጣቸው እግዚአብሔር ስለ ሆነ ነው።

12. ሁሉንም ትእዛዛት እየጠበቁ አንዷን እንኳን ስለመተላለፍ እግዘብሔር ምን አለ?

ሀ- እግዘብሔር ሁሉንም ትእዛዛት እንደ መተላለፍ ነው አለ።

13. አሥርቱን የእግዚአብሔር ትእዛዛት አለመጠበቅ የሚያስከትለው ቅጣት ምንድን ነው?

ሀ- ሞት ይኸውም በዘላለሙ ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

14. የእግዚአብሔር ትእዛዛት እንደ መስተዋት የሆኑት እንዴት ነው?

ሀ- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ኃጢአታችንን እንድናይ ስለሚያግዙን ነው።

ለ- የእግዚአብሔር ትእዛዛት ኃጢአታችንን ስለሚያሳዩን ነው።

15. እግዚአብሔር ትእዛዛቱን ለምን ሰጠን?
ሀ- ቆሻሻውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን እንዲያሳዩን።

16. የቆሸሸውንና ኃጢአተኛውን ልባችንን ማንጻት የሚችል ማን ብቻ ነው?
ሀ- እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እስራኤላውያን አሥርቱን ትእዛዛት እንዲረሱ ስላልፈለገ እግዚአብሔር ራሱ በሁለት ጽላቶች ላይ ጻፈላቸው።

- በሁለቱ ጽላቶች ላይ የጻፋቸውን ትእዛዛት እንዲወስድለት እግዚአብሔር ወደ ሲና ተራራ ላይ ሙሴን ጠራው።

ዘጸአት 24፡12

12- እግዚአብሔር ሙሴን፣ «በተራራው ላይ ወደ እኔ ና፤ በዚህም ቆይ፤ እኔም መመሪያ እንዲሆናቸው ሕግና ትእዛዛት የጻፍኩባቸውን የድንጋይ ጽላቶች እሰጥሃለሁ» አለው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ታዝዞ ወደ ሲና ተራራ ወጣ።

- ኢያሱ የሚባል ወጣት ከሙሴ ጋር ሄደ።

ዘጸአት 24፡13-15 & 18

13- ከዚያም ሙሴ ከረዳቱ ከኢያሱ ጋር አብሮ ሄደ፤ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጣ።

14- እርሱም ሽማግሌዎችን፣ «ወደ እናንተ እስክንመለስ ድረስ በዚህ ቆዩ፤ አሮንና ሖር ከእናንተ ጋር ናቸው፤ ክርክር ያለው ሰው ቢኖር ወደ እነርሱ ይሂድ» አላቸው።

15- ሙሴም ወደ ተራራ ሲወጣ፣ ደመናው ተራራውን ሸፈነ፤

18- ከዚያም ሙሴ ወደ ተራራው ደመናው ውስጥ ገባ፤ በተራራው ላይ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ቆየ።

- ሙሴ ከተራራው ላይ እንደ ደረሰ እግዚአብሔር ዐሥርቱን ትእዛዛት ሰጠው።

- እግዚአብሔር ለሙሴ ዐሥርቱን ትእዛዛት በሰጠበት ጊዜ ሙሴ አንድ ነገር እንዲሠራለት አዝዞት ነበር።

- ሙሴ እንዲሠራለት እግዚአብሔር ያዘዘው ነገር ምንድን ነው?

- እግዚአብሔር ሙሴ የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠራ አዘዘው።

ዘጸአት 25፡8

8- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «ከዚያም መቅደስ እንዲሠሩልኝ አድርግ፤ እኔም በመካከላቸው አድራለሁ።»

- እግዚአብሔር ሙሴ ድንኳን እንዲሠራለት ያዘዘው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት ያስፈልገዋል?

- አያስፈልገውም።

- ለእግዚአብሔር የሚኖርበት ቤት የማያስፈልገው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ ስለሚገኝ ነው።

- ታዲያ ሙሴ ድንኳን እንዲሠራለት እግዚአብሔር የጠየቀው ለምን ነበር?

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ታስታውሳላችሁ?

- እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ቃል ኪዳን ምን ነበር?

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በሙሉ የሚጠብቁ ከሆነ እግዚአብሔር ምን ሊያደርግላቸው ቃል ገባ?

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ የሚጠብቁ ከሆነ እንደሚባርካቸው።

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ የማይፈጽሙ ከሆነ እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግባቸው ተናገረ?

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ የማይጠብቁ ከሆነ እንደሚቀጣቸው።

- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ መጠበቅ ችለዋል?
- አልቻሉም።

- እስራኤላውያን ትእዛዛቱን ሁሉ መጠበቅ እንደማይችሉ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር?

- አዎን።

- ከትእዛዛቱ አንዱን እንኳን ለሚጥሱ የእግዚአብሔር ቅጣት ምንድን ነው?

- ሞት በዘላለሙ ባሕር ውስጥ መጣል ነው።

- እግዚአብሔር ሙሴ ድንኳን እንዲሠራለት የፈለገበት ምክንያት ይህ ነው፡

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለሚወድድ በእሳት ባሕር ውስጥ እንዲጣሉ አልፈለገም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን በዘላለሙ የእሳት ባሕር ውስጥ እንዲጣሉ ስላለፈለገ የማምለጫ መንገድ አዘጋጀላቸው።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያዘጋጀላቸው የማምለጫ መንገድ ምን ነበር?

- እስራኤላውያን ኃጢአት በመስራት ከእግዚአብሔር ሕግጋት አንዱን በሚጥሱበት ጊዜ ሁሉ ወደ መገናኛው ድንኳን ሄደው የእንስሳት ደም ያቀርባሉ።

- እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ምን ያደርጋል?

- እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ለኃጢአት የተሻለ ዋጋ እስኪከፈል ድረስ እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀባል።

- እግዚአብሔር ሙሴና እስራኤላውያን ድንኳኑን እንዴት እንዲሠሩለት ፈለገ?

ዘጸአት 25፡9

9- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «የማደሪያ ድንኳኑንና በውስጡ ያለውን ዕቃ ሁሉ ልክ እኔ በማሳይህ ዕቅድ መሠረት ሥሩት። »

- እግዚአብሔር ሙሴና እስራኤላውያን ድንኳኑን እንዲሠሩለት የፈለገው እንዴት ነበር?

- ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት።

- ኖኅ መርከቡን በምን መልክ እንዲሠራ ነበር እግዚአብሔር የፈለገው?

- ልክ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት።

- ኖኅ መርከቡን እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት እንዲሠራ እንዳዘዘው ሁሉ ሙሴም የማደሪያውን ድንኳን እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት እንዲሠራ እግዚአብሔር አዘዘው።

- ወደ እርሱ እንዴት መቅረብ እንዳለብን ለእግዚአብሔር ልንነግረው አንችልም።

- ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምንችለው፥ እርሱ በሚነግረን መንገድ ብቻ ነው።

- በራሳችን መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አንችልም።

- ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምንችለው በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።

- የእግዚአብሔርን መንገድ የምንማረው ከየት ነው?
- ከእግዚአብሔር መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ድንኳኑን እንዲሠሩለት የፈለገው በምን አይነት ዕቃዎች ነው?
- ከእንስሳት ቆዳና ከፍየል ጸጉር በተሠሩ ዕቃዎች።

- ከዚያም እግዚአብሔር ሁለት ክፍሎችን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲሠራ ሙሴን አዘዘው።

- እግዚአብሔር ሙሴ በመገናኛው ድንኳን ውስጥ እንዲሠራ ያዘዛቸው ሁለት ክፍሎች ምንና ምን ይባሉ ነበር?

- ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ይባሉ ነበር።

- የመጀመሪያው ክፍል ቅድስት ይባል ነበር።
- ያ ክፍል ለእግዚአብሔር የተለየ ነበር።

- ወደ መጀመሪያው ክፍል መግባት የሚችሉት ጥቂት ሰዎች ብቻ ነበሩ።

- ሁለተኛው ክፍል ቅድስተ ቅዱሳን ተብሎ ይጠራል።
- ይህ ክፍል የእግዚአብሔር ብቻ ነበር።

- ወደዚህ ክፍል በዓመት አንድ ጊዜ መግባት የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ነበር።

- ምክንያቱም የእግዚአብሔር ክብር በዚህ ክፍል ውስጥ ስለሚሆን ነበር።

- እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት የመገናኛውን ድንኳን የሚሠሩለት ከሆነ የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ይገባል።

- ቀጥሎም እግዚአብሔር ሙሴ ልዩ ሳጥን እንዲሠራና በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እንዲያስቀምጥ አዘዘው።

- ልዩው ሳጥን የቃል ኪዳን ታቦት በመባል ይታወቃል።

ዘጸአት 25፡10-11

10- እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው] «[እስራኤላውያን] ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል፣ ከፍታው አንድ ክንድ ተኩል የሆነ ታቦት ከግራር እንጨት እንዲሠሩ አድርግ።

11- ውስጡንም ውጭውንም በንጹሕ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ ክፈፍ አብጅለት።»

- እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ከልዩ ዓይነት ዛፍ እንጨት እንዲሠራ አዘዘ።

- እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት በወርቅ መለበጥ እንዳለበት አዘዘ።

- እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ታቦት ርዝመት ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል ከፍታው አንድ ክንድ ተኩል እንዲሆን አዘዘ።

- ቀጥሎም እግዚአብሔር ሙሴን ለቃል ኪዳኑ ታቦት መሸፈኛ እንዲሠራ አዘዘው።

ዘጸአት 25፡17

17- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ከንጹሕ ወርቅ ሥራለት።»

- እግዚአብሔር ሙሴን የቃል ኪዳኑ ታቦት መሸፈኛን ከንጹሕ ወርቅ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር መሸፈኛው ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱ አንድ ክንድ ተኩል እንዲሆን አዘዘ።

- ይህ መሸፈኛ የሚሆነው የእግዚአብሔር ክብር በሚገኝበት በእስራኤላውያን መካከል ነበር።

- ቀጥሎም እግዚአብሔር ሙሴን ለመሸፈኛው ሁለት የመላእክት ምስል ከወርቅ እንዲሠራ አዘዘው።

ዘጸአት 25፡18-20

18- እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው «በስርየት መክደኛው ዳርና ዳር ላይ የሚሆኑ ከወርቅ የተቀረጹ ሁለት ኪሩቤል ሥራ።

19- አንዱን ኪሩብ በአንደኛው፣ ሁለተኛውን ኪሩብ በሌላኛው ዳር አድርግ። በሁለቱም ጫፎች ሁለቱን ኪሩቤል ከስርየት መክደኛው ጋር አንድ ወጥ አድርገህ ሥራቸው።

20- ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ በመዘርጋት የስርየት መክደኛውን በክንፎቻቸው ይሸፍኑ፤ እርስ በርሳቸው ትይዩ በመሆንም ፊታቸውን ወደ ስርየት መክደኛው ያድርጉ።»

- እግዚአብሔር ሙሴን በአንደኛው የስርየት መክደኛ ጫፍ አንድ የመልአክ ምስል በሌላኛው ጫፍ ሌላ የመልአክ ምስል ከወርቅ እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ሁለቱ የመላእክት ምስሎች ፊት ለፊት የሚተያዩ ክንፎቻቸው ተዘርግተው የስርየቱን መክደኛ የሚሸፍኑና ፊታቸው ወደ ታች የሚመለከቱ ሆነው እንዲሠሩ አዘዘ።

- ቀጥሎም እግዚአብሔር ሙሴን የስርየቱን መክደኛ በቃል ኪዳኑ ታቦት ላይ እንዲያኖር አዘዘው።

ዘጸአት 25፡21-22

21- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «የስርየት መክደኛውን በታቦቱ አናት ላይ አስቀምጠው፣ እኔ የምሰጥህን ምስክሩንም በታቦቱ ውስጥ አስቀምጥ።

22- በምስክሩ ታቦት ላይ ባሉት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል፣ በስርየት መክደኛው ላይ በዚያ እኔ ከአንተ ጋር እገናኛለሁ፤ ለእስራኤላውያን የሚሆኑትን ትእዛዞቼንም እሰጥሃለሁ። »

- እግዚአብሔር ሙሴ አሥርቱን ትእዛዛት የተጻፈባቸውን ሁለት ጽላቶች በቃል ኪዳኑ ታቦት ውስጥ እንዲያስቀምጥ አዘዘው።

- የእግዚአብሔር ክብር ከእስራኤላውያን ጋር የነበረው ከሁለቱ መላእክት ምስሎች መካከል ባለው የስርየት መክደኛው ላይ ነበር።

- በተጨማሪም እግዚአብሔር ቅድስቱንና ቅድስተ ቅዱሳኑን በመጋረጃ እንዲከፍል አዘዘው።

ዘጸአት 26፡31 & 33

31- እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ አለው «ከሰማያዊ፣ ከሐምራዊ፣ ከቀይ ማግና በቀጭኑ ከተፈተለ በፍታ መጋረጃ አብጅ፤ እጀ ብልህ ሠራተኛም ኪሩቤልን ይጥለፍበት።

33- መጋረጃውን በማያያዣዎቹ ላይ ስቀለው፤ የምስክሩንም ታቦት ከመጋረጃው በስተኋላ አስቀምጠው፤ መጋረጃውም መቅደሱን ከቅድስተ ቅዱሳኑ ይለያል። »

- ቅድስትንና ቅዱስተ ቅዱሳኑን የሚለየው መጋረጃ ምንን ያመለክት ነበር?

- መጋረጃው እስራኤላውያን በኃጢአታቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየታቸውን ያስተምር ነበር።

- መጋረጃው ቅድስተ ቅዱሳኑን ከቅድስት እንደለየው ሁሉ ኃጢአት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ይለያል።

- የመጋረጃው ሥራ ሲጠናቀቅ እግዚአብሔር ሙሴ የቃል ኪዳኑን ታቦት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲያስገብስው አዘዘው።

- እግዚአብሔር ሙሴ በድንኳኑ ዙሪያ አጥር እንዲሠራ አዘዘው።

- እግዚአብሔር ሙሴ በአጥሩ ውስጥና ከድንኳኑ ፊት ለፊት ከእንጨት ተሠርቶ በነሐስ የተለበጠ መሠዊያ እንዲሠራ አዘዘው።

ዘጸአት 27፡1-2

1- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «ከፍታው ሦስት ክንድ የሆነ መሠዊያ ከግራር እንጨት ሥራ፤ ርዝመቱ አምስት፣ ስፋቱም አምስት ክንድ ሆኖ ባለ አራት ማእዘን ይሁን።

2- ቀንዶቹና መሠዊያው አንድ ወጥ ይሆኑ ዘንድ በአራቱም ማእዘኖች ላይ ቀንድ አድርግለት፤ መሠዊያውንም በነሐስ ለብጠው።»

- እስራኤላውያን ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ እንስሳ እንዲታረድ በነሐሱ መሠዊያ አጠገብ እንዲያመጡ እግዚአብሔር አዘዘ።

- እስራኤላውያን እንስሳትን እንዴት ማረድ እንዳለባቸው እግዚአብሔር

የተናገረው ቃል ይህ ነው፡

ዘሌዋውያን 1፡4

4- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «የሚቃጠል መሥዋዕት ሆኖ በሚቀርበው እንስሳ ራስ ላይም እጁን ይጫን፤ ይህም ያስተሰርይለት ዘንድ በምትኩ ተቀባይነት ያገኛል።»

- እስራኤላዊው እጁን ለመሥዋዕት በሚያቀርበው እንስሳ ላይ እንዲጭን ከዚያም እንዲያርደው እግዚአብሔር አዘዘ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን በቅድሚያ ለመሥዋዕት በሚያቀርቡት እንስሳ ራስ ላይ እጃቸውን እንዲጭኑ ያዘዘው ለምን ነበር?

- እስራኤላዊው ለመሥዋዕት በሚያቀርበው እንስሳ ራስ ላይ እጁን የሚጭነው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራቱንና ሞት የሚገባው መሆኑን ለመግለጽ ነገር ግን እግዚአብሔር የሰውየውን ሳይሆን የእንስሳውን ሞት እንዲቀበል ነበር።

- የእንስሳት ደም የእስራኤላውያንን የኃጢአት ዋጋ መክፈል ይችላል?
- አይችልም።

- ካልቻለ እግዚአብሔር ለምን ነበር እስራኤላውያን ስለ ኃጢአታቸው እንስሳትን እንዲሠዉ የጠየቃቸው?

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የኃጢአት ቅጣት ሞት መሆኑን ሊያስተምራቸው ስለ ፈለገ ነበር።

- እግዚአብሔር የእንስሳትን ደም በሚያይበት ጊዜ ምን ያደርግ ነበር?

- እግዚአብሔር የእንስሳቱን ደም በሚያይበት ጊዜ ፍጹም የሆነ የደም መሥዋዕት እስከሚቀርብበት ጊዜ ድረስ እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀብ ነበር።

- ቀጥሎም እግዚአብሔር ሙሴ ወንድሙን አሮንን ሊቀ ካህን አድርጎ እንዲሾመው አዘዘው።

- እግዚአብሔር ሙሴ የአሮንንም ልጆች ካህናት አድርጎ እንዲሾማቸው አዘዘው።

ዘጸአት 28፡1

1- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «ካህናት ሆነው ያገለግሉኝ ዘንድ ከእስራኤላውያን መካከል ወንድምህ አሮንን ከወንዶች ልጆቹ ከናዳብ፣ ከአብዩድ፣ ከአልዓዛርና ከኢታምር ጋር ወደ አንተ አቅርባቸው።»

- እግዚአብሔር አሮንንና ልጆቹን ካህናት አደረጋቸው።

- ነገር ግን ሊቀ ካህኑ አሮን ብቻ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን እንዲገባ ተፈቀደለት።

- አሮንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲገባ ተፈቀደለት።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ሁሉንም ኃጢአት ስለሚጠላ ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚችለው በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር።

ዘሌዋውያን 16፡2

2- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «እኔ በስርየቱ መክደኛ ላይ በደመና ውስጥ እገለጣለሁና፣ ወንድምህ አሮን በመጋረጃው ውስጥ ወዳለው ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ማለት በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ስርየቱ መክደኛ ፊት፣ በፈለገ ጊዜ ሁሉ እንዳይገባና እንዳይሞት ንገረው።»

- አሮን በፈለገው ጊዜ ሁሉ ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ ቢገባ ምን ይሆናል?

- ይሞታል።

- አሮን ወደ ቅድስተ ቅድሳኑ የሚገባው እግዚአብሔር በመረጠው ቀን በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር።

- አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ እንዲገባ እግዚአብሔር የመረጠበት ቀን ሲደርስ ምን ይዞ እንዲገባ አዘዘው?

ዘሌዋውያን 16፡14

14- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው «ከወይፈኑም ደም ወስዶ በስርየቱ መክደኛ ፊተኛው ወገን ላይ በጣቱ ይርጭ፤ ደግሞም በስርየቱ መክደኛ ትይዩ በጣቱ ሰባት ጊዜ ይርጭ።»

- እግዚአብሔር አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን በሚገባበት ጊዜ የእንስሳ ደም ይዞ እንዲገባ አዘዘው።

- አሮን በእንስሳው ደም ምን ያደርግበታል?

- ደሙን በቃል ኪዳኑ ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ ይረጨዋል።

- እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነና ኃጢአትን ሁሉ ስለሚጠላ ሊቀ ካህኑ የእንስሳት ደም ይዞ በቅድስተ ቅዱሳኑ ውስጥ በሚገኘው የኪዳኑ ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ ይረጨዋል።

- እግዚአብሔር ያዘዘውን አሮን ካደረገና በኪዳን ታቦት የስርየት መክደኛ ላይ ደም ከረጨ እግዚአብሔር ምን ያደርጋል?

- እግዚአብሔር የተሻለ የኃጢአት መሥዋዕት እስኪቀርብ ድረስ ለተጨማር አንድ አመት እስራኤላውያንን ከመቅጣት ይታቀባል።

- እኛ ወደ እግዚአብሔር እንዴት መቅረብ እንዳለብን ለእግዚአብሔር መንገር አንችልም።

- እኛ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብን እርሱ በሚነግረን መንገድ ነው።

- በራሳችን መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አንችልም።

- ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚገባን በእግዚአብሔር መንገድ ብቻ ነው።